የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

የካቲት 23/2003

## <u>በሊቢያ ያሉ ስድስት ዜጎች መገደላቸው ተገለፀ</u>

በትሪፖሊ ከተማ ብቻ ስድስት ኢትዮጵያውያን በወጡበት እንደቀሩና ተገድለዋል መባሉ
ለኢፖእአኮ ተገልጿል፡፡ ከትሪፖሊ በስልክ ለኢፖእአኮ ገለፃ የሰጡት ዜጎች ብዙዎች በረሀብና በስጋት
ም እየተጠቁ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ በረሀ እስር ቤቶች ታግተው ያሉት የብዙ ሀገሮች ስደተኞ
ችም ዕጣ በጣም አሳሳቢ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡

የሌሎች ሀገሮች ስደተኞች በመርከብ ወደ ማልታና ወደ ሌሎች ቦታዎችም እየተወሰዱ መሆናቸው
ሲገለጥ ወያኔ ግን በጉዳዩ ላይ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የቀጠለ መሆኑም ታይቷል፡፡ የወያኔ ቅጥረኞችና
ታዛዦች ግንስደተኛው ወደ ኢትዮጵያ እንደሚለስ ለማድረግ እየተፍጨረጨሩ መሆናቸውን
ለማወቅ ተችሏል፡፡ አንዳንድ ዜጎች የመለስን አገዛዝ ያጋለጡ እየመሰላቸው ነጋ ጠባ የኢትዮጵያ ወታደ
ሮች ለጋዳፊ ተሸጠው ሊቢያኖችን እየገደሉ ነው በሚል የሚያስተጋቡት ያልተረጋገጠ ወሬና ክስ የስደ
ተኞቸን ይዞታ ለአደጋ ይበልጥ እያጋለጠ በመሆኑ ኢፖእአኮ ይህ ጥንቃቄ የጎደለው ስራ በአስቸኳይ
ይቁም ይላል፡፡ የክሱ ሀቅንት ራሱአከራካሪ ከመሆኑ ሌላ በየቴሌቪዥኑ ኢትዮጵያውያን እየገደሏችሁ
ነው የሚለው ጩኸት ወገኖቻችን ለብቀላ ግድያ የሚያጋልጥ ነው፡፡ በተለይም የሊቢያ ህብረተ ሰብ ፀረ
አፍሪካውያን አቅዋምና ዘረኝነት የታወቀ ነውና፡፡

ስደተኞቹን ለመታደግ በየአቅጣጫው ዜጎች የጀመሩት እንቅስቃሴ (በቀይ መስቀል አማካኝነት ወደ
ጣሊያን ለመውሰድ የሚደረገውን ሙከራ ጨምሮ) የሚበረታታ ቢሆንም ሁኔታውን ለራሳቸው ትርፍ
ለመጠቀም በተለይ በአውሮጳ የታወቁ ሕፃናትና ስደተኞችን አመላላሽ/ሻጭ ክፍሎች እርዳታ አሰባሳቢ
መስለው የጀመሩትን እንቅስቃሴ ማጋለጥና ማስቆምም ያስፈልጋል፡፡ ኢፖእአኮ በሊቢያ ያሉትን ዜጎች
ከመከራና ሞት ለማዳን የተቻለውን ሁሉ ከሌሎች በመተባበር እየጣረ መሆኑን ይገልፃል፡፡

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM